# በጀ! የሠራዊቱ አዛዥ(ኮማንደር) ማን ይሆን?
## አዲዮስ ሠላማዊ ትግል! ቻው ቻው
### ክፍል 2 (ከአያልነሽ)

ግምገማ! ግምገማ! ግምገማ! ምን ዓይነት ግምገማ?
አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በሰሞኑ ባለ 23 ገጽ የግምገማ ጽሁፋቸው ላይ ''ለወደፊቱ ትግል ማመላከቻ የምርጫ 97 አጭር ግምገማ'' ገጽ 1 የግረጌ ማስታወሻቻው ላይ እንዲህ ይላሉ፥

> ''በነገራችን ላይ 'ድክመት' እያልን በዚህ ፅሁፍ ውስጥ የምነጠቀማቸውን ጉዳዮች፣ በተለምዱዊ አማርኛ ስሜቱ፤ ለወቀሳ መንደርደሪያ አድርገን ከመውሰድ መታቀብ እንዳለብን ማስታወስ እንወዳለን። ከዚያ ይልቅ በአውንታ የግምገማ ስሜቱ ለወደፊት ለሚነደፍ የተግባር እንቅስቃሴ መንደርደሪያ የሚሆን፣ የተልምዶ መድበል ተደርጎ ሊወሰድ ይገባል'' ይላሉ።

ደግ ብለዋል አቶ አንዳርጋቸው። እንዳሉት የምራቸውን ከሆነ በአውንታዊ ማየት ደግ ነገር ነው። ያቻችላል፣ ያግባባልም። ታዲያ ''ለመቻቻል'' ሆነ ለመግባባት ''ውኃን ከጥሩ ነገርን ከሥሩ'' ነውና ነገሩ ሁሉ ከሥር መሠረቱ ተጅምሮ ሰከን ባለ፣ በሆይ ሆይታ ሳይሆን ምራቅን በዋጠ፣ በባዶው በሚተከተክ የጥላቻ ስሜት/ትኩሳት ሳይሆን በሰከነ አንደበት፣ ከዚያም ከዚህም በሚዘልና በሚርገጥ ወይም በሚቃረም ኃሳብ ሳይሆን፣ በራስ ከሚተማመንና ከሚያፈልቅ የተረጋጋ እዕምሮና ሰብዕና ሲመነጭ፣ ጨዋታው ሁሉ ለዛ ይኖረዋል። አድማጭና ታዛቢም ነገሬ/ጉዳዩ ብሎ ያዳምጠዋል፤ ጆሮም ያገኛል። ሰክኖ ወይ ረግቶ የሚጨዋወቱት ጨዋታ ደግሞ በዓይን ይግባል ይባላልም።

አቶ አንዳርጋቸውን ቅር የማላሰኝ ከሆነ በደረስንበት ዘመን ''ዘመናዊው ፖለቲካ'' ነገሩን ሁሉ አዘበራርቆ፣ አደበላልቆብናልና ብንቸገር (በመቸገራችን) ሊያዝኑብን፣ ሊቆጡብን፣ ሊበሳጩብን አይገባም። በተጨማሪ ቁጣና ብስጭት ደግሞ ራስን ጎጅ ከመሆኑ ሌላ ኃሳብን በአግባቡና በመልኩ ለማስቀመጥ የሚመች አይደለም፣ ገላጭም ሊሆን አይችልም። ግምገማ! ግምገማ! ግምገማ! ምን ዓይነት ግምገማ? አዎ! ግምገማ ከተባለ አሉታዊ ሳይሆን አወንታዊ፣ አገርና ሕዝብን የሚጎዳ ሳይሆን አገርና ሕዝብን የሚጠቀም፣ በመናኛ ነገር ሳይሆን በሚጨበጥና በሚታይ፣ በሰዎች ሰብእና ላይ ሳይሆን ሰዎች በተናገሩትና በሚናገሩት ይዘት ላይ፣ ሰውን ለመጉዳት ወይ በሰዎች ስቃይ ለመደሰት ሳይሆን፣ እንደ ሰው ለሰው ልጆች በሚሰጥ ክብር ሲባል የሚደረግ አወንታዊ ''ግምገማ'' ጠቃሚነቱ አያጠያይቅም። በዘህ መመዘኛ ላይ የተመሰረተና የቆመ ''ግምገማ'' ሌላ ቅፅል ወይ ድሪቶ አያስፈልገውም። ''ግልጽነትና ተጠያቂነት፣ ተሃድሶና ተወድሶ'' የሚል አቃቂርንም የሚጠይቅ አይሆንም።

በበሰለ የፖለቲካ ክርክርና ጥልቀት ባለው የሰከነ ውይይት፣ እንዲሁም በሚታይና በሚጨበጥ ጉዳይ፣ መሬት ላይ ባለ ፖለቲካዊ ትንታኔና ይዘት ላይ ተከራክሮ ማስተማር፣ማስጨበጥ ሲቸግር፣ ብቃት፣ችሎታ፣ ጥራት ሲጎድልና ሲያንስ፣ ከጥልቁና ከረቂቁ የፖለቲካ ጨዋታ ውስጥ ቃሎችን ነጥሎ በማውጣት፣ የቃላትና የፀጉር ስንጠቃ አባወራ

መሆን፣ የቃላት ጨዋታ እንጅ፣ ረቂቁን የፖለቲካ ዚቅ መጨበጥን ወይም መገንዘብን አያመላክትም። አዋቂዎች እንደሚሉት ፖለቲካ ሳይንስ ነው። ሳይንስ ራሱ ደግሞ ጥበብና ረቂቅ ነገር ነው። በመሆኑም እንደ እቃ ግዥ በዘፈቀደ የሚዘግኑት ወይ የሚገዙት ወይም ዘው ብለው የሚገቡበት ነገር እንዳልሆነም ፖለቲካ ሳይንሱ ያስተምራል።

አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ እንደሚያውቁት በህወኃት/ ወያኔ፣ በኢህዴን/ኢህአዴግ የፖለቲካ ፍልስፍናና ዕምነት፣ "ግምገማ" ዋናና ዓይነታ የቡድኑ መሳሪያ ነው። በዚሁ ዓይነተኛ መሣሪያው የወያኔ/ኢህአዴግ "ግምገማ" ብዙ ተገምጋሚዎችን ገምግሞ ዘርሯል። የኢሕዴን/ብአዴን/ኢህአዴግ ዋና ሰውና፣ የአቶ አንዳርጋቸው የቅርብ ሰው የነበሩት ታምራት ላይኔ የመጀመሪያው ተገምጋሚ ሰው ሆነው፣ ዋጋቸውን ሰጥቷቸዋል፤ ግምገማ። የኢሕዴን/ብአዴን ነባር አባሎችን "ግምገማው" እያሳደደ መንጥሯል። የአቶ አንዳርጋቸው ድርጅት የነበረው ኢህዴን/ብአዴን ውስጥም ቱባ ቱባ ሰዎችን፣ ጥግ አስይዟል፤ አሊያም በወያኔው አለቃ በለገሰ ዜናዊ ጭብጥ ውስጥ አስተኝቷል። ይሄ እውነት ነው። ይሄ ሆኖ እያለ ታዲያ ሆደ ሰፊው አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ ወያነ/ኢሕአዴግን እስከአሁን ድረስ በክፉ ዓይን አይተውት አያውቁም። ይልቁንም ወያኔን ጠላት የሚልባቸው፣ የአቶ አንዳርጋቸው ቁጥር አንድ ዋና ጠላት ነው። ይብላኝ ለኢሕአፓ! ኢሕአፓን አያድርገኝ መጥኔ!። እሱ ነዋ ወያኔን ጠላት ጠላት እያለ የሚያሳብቅ። ጠላት ያልሆነውን፣ "የሠላሙን ንጉሥ፣" የኢትዮጵያን ወዳጅ ወያኔን!

የ"ግምገማው' ባላባት የሆነው ወያኔ ይህንን መሣሪያውን "ግምገማውን" ተሃድሶ ብሎም ያሽሞነሙነዋል፤ ተሃድሶ" የሚል ስምም አልብሶታል። ደስ አይልም? በዚሁ "ዘመናዊ ወያኔአዊ ግምገማ" ከሥራው የተፈናቀለውንና ሥራ አጥ ሆኖ ከእነ ቤቴሰቡ ለልመና የተዳረገውን ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ፣ በኢትዮጵያችን ቤቱ ይቁጠረው። ይሄ ሁሉ "የግምገማ" ወይ "የተሃድሶው' የሥራ ውጤታችን ነው፤ እንደ ዘንድሮው ዘመናዊው ግምገማ "ግልፅነትና ተጠያቂነት" ዓይነት መሆኑ ነው። ደግ ነገር! ለመሆኑ በቁም ነገር "ተወያዩበት" ባሉን ወረቀትና በፓል ቶክ ላይ በአስተላልፉት መልዕክታቸው የአቶ አንዳርጋቸው ቅንጅት ሲገፋ የቀየውን "የሠላማዊ ትግል" ድንገት ዛሬ አውግዞ የትጥቅ ትግልን ሲያውጅ፣ የዚህ የትግል-ስልት መነሻውና መድረሻው የት ነው? የአቶ አንዳርጋቸው የትጥቅ ትግል ጥሪስ ዒላማ ያደረገው ማንን ነው? ያነጣጠረውስ በማን ላይ ነው? ማን ነው ጠላት? ማን ነው ወዳጅ? እንደሚታወቀው በአቶ አንዳርጋቸው ድርጅት የቅራኔ አፈረጃጀት ላይ በ"ማንፌስቶው" እንደተተነተነውና በአደባባይ በኩራት እንደሚነገረው ፣ ወያኔን በጠላትነት የማያየው መሆኑንና ጠላት ነው ብሎ እንደማያምን፣ እንደማይቀበልም ነግሮናል ደጋግሞ፤ ይሄ ግልጽ ነው።

ታዲያ ይህ የትጥቅ ትግልና የሁለ ገብ ትግል ጥሪ "ጠላት" በሌለበት አገር፤ በማን ላይ ያነጣጠረና የሰበቀ ነው? የውጭ ወራሪን ለመምታት ? ወይስ እንደሳቸውና እንደ ወዳጃቸው ወያኔ/ኢህአዴግ በጎጤ አላሰብም፣ ኢትዮጵያዊነትን በዘሬ አልመነዝርም ባለው ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊነት ላይ የተሳለ ሰይፍ? ወይስ በኢሕአፓ (በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ) ላይ? ወይስ በመኢአድ (በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት) ላይ ? ወይንስ "በአምባገነኑ" ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል ላይ? አቶ አንዳርጋቸው እባክዎ ይብራራ። ሌላም ተጨማሪ ጥያቄ አለኝ አብሮ ተያይዞ ሊመለስ ይችላል። ይህ የትጥቅ ትግል የሚጀመረው መቼ ነው? የሚጀመርበትስ? በሰሜን፣ በደቡብ፣ በምስራቅ ወይስ በምዕራቡ

"ክልላችን"? በየትኛው በኩል ይሆን? የጥያቄዎቼ መነሻ "ግልጽነትና ተጠያቂነት" በሚለው ጽኑ መርኃችን መሰረት ላይ ቆሜ ነው፤ ግን ከታላቅ ይቅርታ ጋር። በወያነ/ኢሕአዴግ "ግምገማ" የተመነጠሩት የኢህዴን/ብአዴን አባሎችስ የዚሁ የአዲሱ የትጥቅ ትግል ጥሪ መሪ ተዋንያን ይሆኑ ይሆን? ድንገት "በኢሕአዴጉ ግምገማ" የተመነጠሩት የቀድሞ ብአዴን አባላት ብዙ ናችውና ብዬ ነው። "በተመክሮ" ከሚልም የጀማሪው ሠራዊት አስኳል ቢሆኑስ። እስቲ "በግልጽነት" እንወያይ አቶ አንዳርጋቸው። ይህ "ተዋጊ ሠራዊት" ተጠሪነቱ አሁን በቅርቡ ለሚመሠረተው በአቶ አንዳርጋቸው በተነገረንና በታሰበው "በትልቁ ሕብረት" ሥር ይሆን?

የዕዝ ማዕከሉስ የት ነው ? ባህረ ነጋሽ? ባድሜ ? መቀሌ? ፊንፊኔ? ኦጋዴን? ወይስ በአዲሱ 'ክልላችን" በ "ክልል" 15 መቅድሾ/ሶማሌ?። የሠራዊቱ ኮማንደርስ ማን ይሆን? ጀኔራል አንዳርጋቸው ፅጌ? ጀኔራል ሰዬ አብርሃ? ጀኔራል አረጋሽ አዳነ? ጀኔራል ገብሩ አሥራት ወይስ ብርጋዴር ጀኔራል ሙሴ ተገኝ? ማንኛቸው ይሆኑ? ጥያቄዎቼ በእወንታዊ ይታዩልኝ ግን "ግልጽነትንና ተጠያቂነትን" የሚቃረን ከሆነ ላለመመለስ ይቻላል። "ወታደራዊ ምስጢርን" ለጠላት አሳልፎ ላለማጋለጥ ሲባል።

የስንቅና ትጥቁ (ሎጅስቲክ) ዘርፉም ቀላል ስላልሆነና ከዲፕሎማሲ ሥራው ጋርም መያያዙ አይቀረም። ለዚህ ከባድ ኃላፊነትስ የሚመደበው ማን ይሆን? ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ? አቶ ብርሃነ መዋ? አቶ ደበበ እሸቱ? ወይስ ወይዘሮ አያልነሽ ጫኔ ያለው? አስታውሱ! እኝህ እመቤት በብርቱካን ሚደቅሳ መሪነት ወደ አሜሪካ ዘልቆ የነበረውን የዶ/ር ብርሃኑን ቡድን ከልደቱ አያሌው ጋር በማግባባቱ ሥራ ላይ "የተዋጣላችው" ሰው እንደነበሩ፣ ያኔ ሾልከው በወጡ ተባራሪ የሚዲያ ዜና ለጆሮ ደረሰው እንድነበር አይዘነጋም። ድንገት አሁን ደግሞ በእግረ መንገድ አሁን ለሚታሰበው "ትጥቅ ትግል" በሠራዊት ግንባታው ላይ እንዲሠሩ ኃላፊነት ወድቀባቸው ይሆን? ማን ያውቃል። የትጥቅ ትግል እንቅስቃሴ እኮ በጣም ሚስጥራዊና ከባድ የሆነ ተግባር ነው። ለማንኛውም በጉጉት ለምንጠብቀው የሠራዊት እንቅስቃሴ የምንጠየቀው ነገር ካለ የገንዘብም፣ የሰው ጉልበትም፣ ወዘተ. ወዘተ....ቢኖር በተጠንቀቅ ለመጠበቅና ኪሳችንን ሞልተን፣ ጉልበታችንን ፑሽ አፕ አሠርተንና አድንድነን፣ መጠበቅ እንዳለብን ይሰማኛል! እርስዎስ ምን ይላሉ? እንወያይ አቶ አንዳርጋቸው ግድ የለም! ጨዋታ በሰማይ ደጅ አይገኝም ተብሏልና። ከመሰዋታችን በፊት ውይይት አይከፋም። ይቀጥላል....

የህዝብ ድምፅ ይከበር! የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ!
ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!
ቼር ይግጠመን!
አፕሪል 8/ 2008